የሰ/መ/ቁ. 34940

ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዬ - ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በምስ/ሐረ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአወዳይ ከተማ የሰሩትን ቤት ለአባታቸው ትተው ከሄዱ በኋላ አባታቸው ሲሞቱ አመልካች ቤቱን ይዘው ያሉ ስለሆነ እንዲለቁላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ቤት የተሰራበትን ቦታ ባለቤታቸው ከአቶ ዮሴፍ ኡመር ከተባለ ሰው ወስደው በ1969 ዓ.ም ቤቱን የሰሩ በመሆኑ ከ38 አመት በኋላ ሊጠይቋቸው እንደማይችሉ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ቤቱን ከረጅም ጊዜ በፊት የአመልካች ባለቤት ከአመልካች ጋር አብረው ሲኖሩ የሰሩት መሆኑን የግራ ቀኙ ምስክሮች አረጋግጠዋል በማለት ፍ/ቤቱ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ክርክር የተነሣበት ቤት በከሣሽ(ተጠሪ) ስም የተመዘገ በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ይልቀቁ ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ አቤቱታ አቅርበው አቤቱታቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካችም ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት እንዲታረምላቸው አቤቱታ ለሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ የይርጋ ጥያቄ አንስተዋል ወይ? ካነሱ በየፍ/ቤቶቹ ሣይታይ መታለፉ አግባብ ነው ወይ? ተጠሪስ ያቀረቡት ማስረጃ ባለቤትነትን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚችል ነው ወይ? የሚሉትን ነጥቦች ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተባለው ተጠሪ በአወዳይ ከተማ ቤት ሰርተው ለአባታቸው ሰጥተው መሄዳቸውን ገልፀው አባታቸው በ1978 ዓ.ም ሲሞቱ አመልካች ቤቱን ይዘው መቆየታቸውንና ቤቱንም ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላለሆኑ እንዲለቁላቸው ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካችም ቤቱን ባለቤታቸው በ1969 ዓ.ም የሰሩት መሆኑን ገልፀው ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው እይኖሩበት በመሆኑ ተጠሪ አሁን ሊጠይቋቸው እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በዚህ ክርክራቸው በግልጽ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት አይግለፁ እንጂ ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው እየኖሩበት በመሆኑ አሁን ክስ ሊቀርብባቸው የማይችል መሆኑን መግለፃቸው ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መከራክራቸውን ያመለክታል፡፡ አመልካች ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው በመቆየታቸው የገለፁትን ፍሬ ነገር ተጠሪ አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ወደ ፍሬ ጉዳዩ ከመግባታቸው በፊት በአመልካች በኩል የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መርምረው ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጡ ይገባ ነበር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/1/ ይመለክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቤቱን ለአባታቸው ትቼው ሄጃለሁ የሚሉት በ1969 ዓ.ም ነው፡፡ አባታቸው ከዚህ አለም በሞት የተለዩት በ1978 ዓ.ም ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤቱን ለአባቴ ሰጥቼ ሄጃለሁ ካሉበት ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ክስ

እስከተመሰረተበት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ 27 ዓመት ያለፈው ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱን ለአባታቸው በአደራ ሰጥተው ለመሄዳቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ይህ ተረጋግጧል ቢባል እንኳን አባታቸው በ1978 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ 17 አመታት አልፋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤታቸው ያለአግባብ በሌላ ሰው ተይዟል በማለት ክስ ማቅረብ የሚችሉት እስከመቼ ነው? የሚለው ነጥብ መታየት ይኖርበታል፡፡ በመሰረቱ ጉዳዩን በቀጥታ የሚመለከት በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ድንጋጌ በሌለ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው የጠቅላላ ውል ህግ ድንጋጌ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን ግንኙነቱ ከውል የመነጨ ባይሆንም ስለውሎች በጠቅላላው የተነገሩት ድንጋጌዎች እንደሚፈጸሙባቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው መብቱን መጠየቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ በ10 አመት ውስጥ ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ይገልፃል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ ቤቱ ያለአግባብ በአመልካች ተይዟል ካሉበት ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ 17 አመታት ያለፉ በመሆኑ የተጠሪ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ አመልካች ከስር ጀምሮ ቤቱን ለብዙ ዓመታት ይዘው እየተጠቀሙ የቆዩ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ እንደሚገባ ተከራክረው እያለ ፍ/ቤቶቹ ይህንን የአመልካችን የይርጋ ክርክር ሳያስተናግዱ በማለፍ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያመለክታል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39769 በ29/02/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በ/ቁ 57751 በ20/3/2000 የሰጠው ትእዛዝ በተጨማሪ በምስ/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01899 በ08/07/98 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ቤት ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ /ክስ/ በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ